# በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ

ታህሳስ፤2013 ዓ.ም

## መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት እና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው እና ካፀደቀቻቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች መሠረት እንደ ትንኮሳ እና ጥቃት የሰብአዊ ጥሰት በመሆኑ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በነፃነት የመማር፣ መልካምና ምቹ የመማሪያ አካባቢ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣

ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ተግባር ቢሆንም፣ በተለይ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑት ሴቶች በመሆናቸው፣ ይኸም የሴቶችን የትምህርት ተሣትፎ ብቃት ውጤታማነት የሚያቀጭጭ በመሆኑ በሃገሪቱ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ባሕላዊ እድገትን ልማት ላይ አሉታዊ ተፅእና ያለው በመሆኑ ፣

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየተፈፀሙ ያሉ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል፣ ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት እንዲሁም የሚፈጸሙ ድርጊት ፈፃሚዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አሁን በስራ ላይ ባለው የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ሕግ ፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት ህጉ፣ የዩኒቨርሲቲው ስርአተ ጾታ ፖሊሲ፣ የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር አዋጅ፣ የሲቪል ሰራተኞች አዋጅ እና የተለያዩ የዲስፕሊን መመሪያዎች ስር የተካተቱትን ደንብ እና መመሪያዎች በሚጠበቀው ደረጃ ከመተግበር ባሻገር ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት በተጠናከረ መልኩ ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና ብሎም ለማጥፋት ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት በዝርዝር የሚዳስስ ራሱን የቻለ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት መመሪያ አስፈላጊ በመሆኑ::

የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስተር በትምህርት ተቋማት የሚፈፀመውን ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል ያወጣን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከዩኒቨርሲቲው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ በማስፈለጉ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ--------------በተሰጠው ስስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃት ለመከላከል የወጣ መመሪያ**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የተፈፃሚነት ወሰን

2.1. ይህ መመሪያ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ የአካዳሚክ ማህበረሰብ ፣ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ የኮንትራት እና የቀን ሠራተኞች መካከል በትምህርት ተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሚፈፀሙ የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ፈፃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:: ሆኖም ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውጭ ቢሆንም ለዩኒቨርሲቲው ስራ እነዚህ ማሕበረሰቦች ሥራ ላይ ከሆኑ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

2.2. ይሕ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሚቀጠሩ ተጋባዥ መምህራን እና ኩንትራት ሠራተኞችም ተፈጻሚ ይሆናል።

## 3. ትርጓሜ

***የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣***

**3.1. ጾታዊ ትንኮሳ፡** - ሌላ ሰዉን ተቀባይነት ወደሌለው ጾታዊ ባህሪ ያለውን ነገር መፋፋት። እንደዚህ ያለ ጠይ ሆነ ብሎ ሌላ ሰዉ ከጾታዊ ነገር ጋር በተሳሰረ መንገድ ማበደል ወይም ጾታዊ በሆነ መንገድ አላስፈላጊ አተኩሮ ማስጠት፣ ማካካት ወይም ዛቻ ማስፈራራት እና ይህ ተግባር ተጠቂዉን ግለሰብ ስላምሲን ሳው፣ ሲያስፈራውወይምበሁኔታውዋስትና ሳይሰማውሲቀር ::

**3.2. ወሲባዊ ጥቃት:-** ማለት ፆታን መሰረት ያደረገ አካላዊ ንክኪ ያለበት የኃይል ጥቃት ነው፡ ፡

3.3. **አስገድዶ መድፈር** ማለት አንድን ሰው ከፈቃዱ/ዷ ውጪ የኃይል ጥቃትንም ሆነ ማስፈራራትን፣ ዛቻን ወይም አደንዛዥ መድሀኒቶችን ወይም ሌላ ማንኛውንም እራሱ/ሷን መከላከል እንዳይችል/እንዳትችል ወይም ፍቃዱ/ዷን እንዳይጠቀም/እንዳትጠቀም የሚያደርግ መንገድ በመጠቀም የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ወይም ለመፈጸም መሞከር ነው፡ ፡

**3.4. ለወሲባዊ ምግባር ፈቃድ** ማለት በግልፅና በቀጥታ የሚደረግ የመስማማት ወይም ያለመስማማት ሀሳብ መግለጫ ሲሆን አንዲት ሴት ፈቃደኝነቷን ቢቻል በንግግር/በጽሁፍ ገልጻ ከተስማማች ብቻ ፈቃዷን እንደሰጠች ይቆጠራል፡ ፡ እንቢ አለማለት ወይም በአካል አለመከላከል ፈቃድን እንደመስጠት አይቆጠርም፡ ፡

**3.5.** በወሲብ ማገድ ማለት አንድ የዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ የሆነችን ሴትን በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በመደለል ወይም በማስማማት ለወሲባዊ ግንኙነት ተግባር ማስማማት ነው፡ ፡ 2.7. አካዳሚክ ማህበረሰብ፣ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሉት ቃላት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 የተሰጣቸው ትርጓሜ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተግባራዊ ይሆናል፡ ፡

3.6. "**ዩኒቨርሲቲ ማለት**" ፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነው

3.7. "አካዳሚክ ማህበረሰብ፣ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች"፣ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም" የሚሉት ቃላት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 የተሰጣቸው ትርጓሜ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**3.8. "ፕሬዝዳንት"** ማለት ፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ነው

3.9. **"የማህበራዊ አገልግሎት"** ማለት፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) (ሐ) መሠረት ቀላል ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ተግባር በፈፀመ ተማሪ ላይ የሚፈፀም የቅጣት አይነት ሲሆን፣ ቅጣቱ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር የአካባቢ ፅዳት፣ አትክልት መንከባከብ ወይም የመመገቢያ ቦታዎችንና እቃዎችን ማጽዳት እና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡

**3.10. "ኮሚቴ"** ማለት ፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተቋቋመው የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ነው፡፡

**3.11. *"ተገቢው ጥበቃ"*** *ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የኮሚቴ አባል ሆኖ እንዲሰራ ለተመደበ ወይም ክስ ላቀረበ ወይም ምስክርነት ለሰጠ የአካዳሚክ ፣ ተማሪ ማህበረሰብ አባል ወይም ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ የሚሰጥ ጥበቃ ሆኖ የሚከተሉትን እርምጃዎች ያካትታል፣*

*3.11.1 ጥበቃ የሚያስፈልገው ተማሪ በሆነበት ጊዜ መምህሩ /የመማሪያ ክፍሉ እንዲለወጥለት ወይም ፈተናው በሌላ አራሚ እንዲታረምለት ማድረግን፣*

*3.11.2 ጥበቃ የሚያስፈልገው መምህር ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ከሆነ የስራ ሃላፊው እንዲቀየርለት ወይም ወደ ሌላ የስራ ክፍል ወይም የስራ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከነዚህ እርምጃዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሌላ ተገቢነት ያለው እርምጃን፣የሚያካትት ነው፡፡*

*3.12. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፁት ቃላቶች ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡*

**4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ የአካዳሚክ ማህበረሰብ (ተማሪ፣ አስተማሪ፣ ተመራማሪ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ አባላት፣ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪሠራተኞች) መካከል በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ወስጥ ለሚፈፀሙ ወሲባዊ ትንኮሳ ተግባራት ፈፃሚዎች ላይ፣ ለአጭርምሆነ ለረጅምጊዜ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የስራ ግንኙነት ያላቸውየግል ኮንትራክተሮችና ሰራተኞቻቸውላይ ጭምር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ በሌላ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ ከሌላኛው ፈቃድ ውጪ ወይም ወሲባዊ ጥያቄን እንደ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ( Quid Pro Quo) የሚቀርብ የወሲብ ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ይዘት ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ ምልክት ማስጠት ተግባር ወይም በአካል ወይም በስነ አእምሮ ላይ የሚፈፀም ጥቃትን ያካትታል፡፡

በዚህ መመሪያ ከላይ ከተጠቀሱት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ወጪበሆኑ ሰዎች የሚፈፀሙማስል ድርጊቶችን የዩኒቨርሲቲው የስርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት ከህግ አገልግሎት ቢሮ ጋር በመተባበር ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል በተለይም ድርጊቱ ድጋፍ በሚ የዩኒቨርሲቲውማህበረሰብአባላት ላይ የተፈጸመበሆነ ጊዜ ሂደቱን ይከታተላል፡፡

በጥፋተኛውላይ በዚህ መመሪያ ማስረት የጥፋተኝነት ወሳኔ መወሰኑና የድስፕሊን እርምጃ መወሰዱ በሀገሪቱ በስራ ላይ የዋሉ ሌሎች ህጎችን ተፈጻሚ ትአያግድም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃቶች አይነቶች

### 5. የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃቶች ተግባራት ዓይነቶች፣

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(1) እና3(2) የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃቶች የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የጾታዊ ትንኮሳ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፣ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ቀላል ጾታዊ ትንኮሳዎች እና ጥቃት የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም የተባበረ የአካዳሚክ ማሕበረሰብ አባል ወይም ድጋፍ ሰጭ ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተመለከቱት የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድበታል፡፡

**5.1.ቀላል የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት አይነቶች፣**

5.1.1. ከማህበረሰቡ ዕሴት ያፈነገጠ በግላጭመቅረብ የሌለባቸዉን ወሲብ ነክ ምስሎችን፣ ፎቶዎችን፣ ፖስተሮችን፣ ዕሁፎችና፣ መጽሔቶችንና ፊልሞችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሌሎች ያለፈቃዳቸው ማሳየት፣

5.1.2. ወሲብ አዘል ሁኔታን የሚያንፀባርቁ ቀልዶች፣ ቧልቶች፣ሃሜቶችን፣ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎች፣ ገጠመኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ ፈፅሞ መገኘት/መናገር/፣

5.1.3. ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ጾታን ማጥላላት፣ ማናናቅና ማንኳሰስ፣

5.1.4. በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ለምሳሌ በሞባይል፣ ኢሜል፣ የማህበረሰብ ግንኙነት ሚዲያችና በመሳሰሉት የወሲብ ምስል፣ የጽሁፍ መልእክት እና ፎቶግራፍ ያለአንዱወገን ፈቃድ ለሌላ ሰውማሳየት ወይምማስተላለፍ፣

5.1.5. አጸያፊ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ አካላትን አጋልጦማሳየት

5.1.6. የአንድ ሰው ፆታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስ የተመለከቱና ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው አስተያየቶች፣ ነቀፌታዎች፣ ያልተፈለጉና አዋራጅ መገለጫዎችን፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን መጠቀም፣

5.1.7. ተግባር ተኮር ትምህርቶች በሚሰጥበት ወቅት ወሲባዊ ድርጊትን በሚያመላክት መልኩ የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ወይም የቃል አስተያየቶችን መስጠት፣

## 5.2. ከባድ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ዓይነቶች፣

5.2.1 በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ፣ በድህረ ገፅ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛን ምስል በመጠቀምና በማስመሰል የሌላን ሰው ወሲባዊ ሕይወት የሚያጋልጡና የሚያንቋሽሹ ተግባራትን መፈጸም፣ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል መይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛን አካላት በመዳሰስ፣ በመተሻሸት፣ ያለፈቃድ በመሳም ወይም ሆን ብሎ ሌሎች ለወሲብ የሚገፋፉ የሰውነት አካል ግንኙነት መፍጠር፣

5.2.2 አንድን ሰው በማንኛውም ቦታ በመከታተል እና በነፃነት የመንቀሳቀስ መብትን በመጋፋት ላይ የስነልቦና ጫና ማሳደር፣

5.2.3 ለትምህርት ውጤት ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ አስቀምጦ መጠየቅ፣

5.2.4 ወሲብ አዘል ድርጊቶችን በማስገደድ ለመፈፀም በማሰብ የትምህርት መሣሪያዎችና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማትና መደበቅ፣

5.2.5 ቀላል የጾታዊ ትንኮሳ በመፈፀም በተወሰደበት የቅጣት እርምጃ ባለመታረም በተደጋጋሚ ቀላል የጾታዊ ትንኮሳዎችን መፈፀም፣

5.2.6 አስገድዶ መድፈር፣

5.2.7 በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃቶች አይነቶች እንዲፈጸም የተባበረ ወይም ያደመ ፣

5.2.8 በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም ቀላል ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት በከባድ የጾታዊ ትንኮሳ ተግባራት ከተመለከቱት የጥፋት ድርጊቶች ጋር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል።

5.2.9. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ከባድ የጾታዊ ተንኮሳ እና ጥቃት ዓይነቶች የፈፀመ የአካዳሚክ ማሕበረሰብ አባል ወይም የድጋፍ ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተመለከቱት የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድበታል።

## ክፍል ሦስት

## 6. የሚወሰዱ የዲስኘሊን እርምጃዎች፣

ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት አይነቶች ከፈጸመ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት የቅጣት አይነቶች አንዱ ተፈጻሚ ይደረግበታል። ሆኖም ድርጊቱ በሌሎች የዩኒቨርሲቲው መመሪያዎች የተሸፈነ ከሆነ ግን የከበደውን ቅጣት የያዘ የዲስኘሊን ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል።

### 6.1 ቀላል ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት አይነቶች በፈፀሙ ላይ የሚወሰድ ቀላል የስነ-ስርዓት እርምጃዎች፣

6.1.1. ተግሳፅ/የቃል ማስጠንቀቂያ፣

የቃል ማስጠንቀቂያዎች የተከሳሽን ጥፋተኝነት ከተረጋገጠ በኃላ ዉሳኔው በግልባጭ የተማሪው ወይም ሰራተኛው የበላይ ሃላፊ እንዲያውቁት ተደርጎ ኮሚቴው ከጥፋተኛው የትምህርት/የስራ ክፍል የበላይ ኃላፊ ጋር በመተባበር የሚፈፀም የቅጣት አይነት ነው።

ይህ የቃል ማስጠንቀቂያ ጥፋተኛው ተማሪ ከሆነ የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ/ዲን የውሳኔው ግልባጭ እንደደረሳቸው ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመሆን የሚፈጽሙት ይሆናል።

ይህ የቃል ማስጠንቀቂያ ጥፋተኛው መምህር ከሆነ የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ/ዲን የውሳኔው ግልባጭ እንደደረሳቸው ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመሆን የሚፈፅሙት ይሆናል።

ይህ የቃል ማስጠንቀቂያ ጥፋተኛው የአስተዳደር/ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ከሆነ የስራ ክፍሉ ኃላፊ የውሳኔው ግልባጭ እንደደረሳቸው ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመሆን የሚፈፅሙት ይሆናል።

ይህ የቃል ማስጠንቀቂያ ጥፋተኛው ከዩንቨርሲቲው ጋር የስራ ግንኙነት ያለው የግል ኮንትራክተር ከሆነ ወይም የኮንትራክተሩ ተቀጣሪ ሰራተኛ ከሆነ ኮንትራቱን የሰጠው ክፍል ኃላፊ የውሳኔው ግልባጭ እንደደረሳቸው ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመሆን የሚፈፅሙት ይሆናል፡

### 6.1.2. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ

ኮሚቴው የተከሳሽን ጥፋት ካረጋገጠ በኃላ ጥፋተኝነቱ በጽሁፍ ማስጠንቀቅያ ይታረማል ብሎ ሲያምን የዉሳኔ ሃሳቡን ከዝርዝር ማብራሪያ ጋር ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል። ይህ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ለጥፋተኛው ተማሪ/አስተማሪ/ሰራተኛ በቀጥታ እንዲሁም ለትምህርት/ስራ ክፍል ኃላፊ በግልባጭ ይላካል፤ በጥፋተኛው የግል ማህደር ውስጥ የሚካተት ይሆናል።

### 6.1.3. የማህበራዊ አገልግሎት

ኮሚቴው የተከሳሽን ጥፋት መርምሮ አጥፊው ቅጣቱ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ የውስጥ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር በማህበራዊ አገልግሎት ቢቀጣ ከስህተቱ ይማራል ብሎ ከገመተ የአካባቢ ፅዳት፣ አትክልት መንከባከብ ወይም የመመገቢያ ቦታዎችንና እቃዎችን ማጽዳት እና ሌሎች የማህበራዊ አገልግሎት ተግባራትን እንዲፈጽም የዉሳኔሃሳብ ያቀርባል፡

### 6.1.4. የደመወዝ ቅጣት፣

ጥፋተኛውየዩንቨርሲቲውሰራተኛ ከሆነ ና በቃል ወይም የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የማይታረም ከሆነ፣ ወይም ተመሳሳይ ጥፋት ወስጥ ደግሞ ከተገኘ የሁለት ወር ደሞዝ ቅጣትን የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ/ዲን የወሳኔው ግልባጭእንደደረሳቸው ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመሆን የሚፈፅሙት ይሆናል፡፡

## 6.2. ከባድ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ዓይነቶች በፈፀሙ ላይ የሚወሰድ ከባድ የስነ-ስርዓት እርምጃዎች፣

6.2.1. *በተማሪዎች ላይ የሚወሰድ ከከባድ የስነ-ስርዓት እርምጃዎች፣*

6.2.1.1. ከአንድ ሴሚስተር እስከ ሁለት አመት ከትምህርት መታገድ፣

6.2.1.2. ተመራቂ ተማሪ ሲሆን ከተመራቂ ተማሪዎች የስምዝርዝር ወስጥ ስሙማስረዝ እንዲሁምየትምህርት ማስረጃን እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ማገዝ

6.2.1.3. ጥፋተኛው ከየትኛውም ተማሪዎች ማህበራትና እንቅስቃሴ አባልነት እንዲሁም መሪነት እስከሚቋቋሸው ማነበት ወይም ለመሳተፍ ከሚደረግ ወድድር ማገድ፡

6.2.1.4. ከትምህርት ገበታ ማሰናበት፣የአስገድዶ መድፈርን ድርጊት የሞከረ ወይም ፈፅሞ የተገኘ ተማሪ ያለምንም ቅድመሁኔታ ከትምህርት ገበታየሚሰናበት ይሆናል

6.2.1.5. በጥፋተኛው ተማሪ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ለጥፋተኛው ተማሪ በፅሁፍ የሚሰጥ ሆኖ ከግል ማህደሩ ጋር ይያያዛል:: በተጨማሪም ለትምህርት ክፍሉ እና ለሬጅስትራር ጽ/ቤት በግልባጭይላካል:: በሌላ በኩል ውሳኔው ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መማሪያ ይሆን ዘንድ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ሁሉ ይለጠፋል::

6.2.2. በዩኒቨርሲቲው መምህራንና ***የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች*** ላይ የሚወሰድ ከባድ የስነ-ስርዓት እርምጃዎች፣

6.2.2.1. ከሦስት-ስድስት ወር ከስራና ደመወዝ መታገድ፣

6.2.2.2. ካለበት የደመወዝ ደረጃ እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ፣

6.2.2.3. ከአካዳሚክም ሆነ ከአስተዳደር ሀላፊነት እስከ ሶስት ዓመት ድረስ ማገድ፣

6.2.2.4. ከሥራ ማሰናበት፣የአስገድዶ መድፈርን ድርጊት የሞከረ ወይም ፈፅሞ የተገኘ መምህር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከትምህርትና ከስራ ገበታ የሚባረር ይሆናል

6.2.2.5. ***በዩኒቨርሲቲው የሚሰሩ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ላይ የሚወሰድ የስነስርዓት እርምጃዎች፣በተመለከተ*** በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 69 እና ቀጥለው በተቀመጡ አንቀንጾች መሠረት የተቀመጡ የቅጣት አይነቶች በዲስፒሊን ኮሚቴ ተጣርቶ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በፕሬዚዳንቱ ይወሰናል፡፡

6.2.2.6. የቅጣት ውሳኔዎች ለጥፋተኛው መምህር በፅሁፍ የሚሰጥ ሆኖ ከግል ማህደሩ ጋር ይያያዛል:: በተጨማሪም ለትምህርት ክፍሉ እና ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንቱ በግልባጭ ይላካል:: ውሳኔው ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መማሪያ እንዲሆን በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ሁሉ ይለጠፋል::

# ክፍል አራት

## 7. የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ፣

7.1. ማንኛውም በዩኒቨርሲቲው፣ ተማሪዎችና መምህራን የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሣ እና ጥቃትን አጣርቶ የውሣኔ ሃሣብ ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት የሚያቀርብ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡ ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ውሣኔ ይሰጣል፡፡

7.2. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ በሚሠሩ ማንኛውም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሣ እና ጥቃት በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የዲስፒሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 77/94 መሠረት የተቋቋመው የዲስኘሊን ኮሚቴ አጣርቶ ለፕሬዚዳንቱ ቀርቦ ይወሰናል፡፡

7.3. በፆታዊ ትንኮሳና ጥቃት የአካዳሚክ ጉዳዮች ፕሬዚዳንት ተከሳሽ ከሆነ የውሳኔ ሃሳብ ለፕሬዚዳንቱ ቀርቦ ይወሰናል፡፡

7.4. ፕሬዝዳንቱ ተከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ኮሚቴው ጉዳዩን አጣርቶ ለትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ጾታ ማኔጅመንት የስራ ሂደት ያቀርባል፣ የስራ ሂደቱም ጉዳዩን አጣርቶ ለትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ከውሳኔ አስተያየት ጋር ያቀርባል፡፡

7.5. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ ማናቸውም ዓይነት ውሣኔዎች አቤቱታ አቅራቢውን ጉዳዩ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ መደበኛ የፍርድ ሂደቶችን እንዳይከተል አያግዱትም፡

# ክፍል አምስት

## 8. የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ አወቃቀር፣

8.1. የጾታዊ ትንኮሳ አጣሪ ኮሚቴ 7 አባላት ይኖሩታል።

8.2. የኮሚቴው አባላት፣

i. የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊ/ ሰብሳቢ
ii. የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ማህበር ተወካይ/ በሴት ተማሪዎች ወይም በመምህራን የተመረጠች ተወካይ/
iii. የተማሪዎች ሕብረት ኃላፊ /ተወካይ
iv. የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ተወካይ፣
v. ተማሪዎች ዲን/ የስራ ሂደት ባለቤት
vi. የህግ አገልግሎት ኃላፊ፣
vii. በአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሚመረጥ አንድ ተወካይ

8.3. የኮሚቴው አወቃቀር የፆታ ስብጥርን ያማከለ መሆን አለበት ፣

### 9. የአባላት መመዘኛ፣

9.1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል፣

9.1.2. በመልካም ስነ-ምግባር የተመሰገነ፣

9.1.3. የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ተግባር ተከሶ ወይም ጥቃት ፈጽሞ ያልተቀጣ፣

9.1.4. ቢያንስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለአንድ ዓመት ያገለገለ፣ መሆን አለበት።

### 10. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር፣

10.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ለአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በሚመለከት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ጥፋት ድርጊት ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት የመመርመርና ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት የውሣኔ ሃሣብ የማቅረብ፣

10.2. ኮሚቴው አቤቱታዎችን ሲመረምር አቤቱታ አቅራቢን፣ ተከሳሽን ወይም ምስክሮችን የመጥራትና የመስማት፣ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች እንደቀረቡለት የማዘዝ ወይም ሰነዱ ባለበት ቦታ ሄዶ የማየትና ሌሎች ለምርመራ ተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ።

### 11. የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

11.1. ኮሚቴው በ15 ቀን አንድ ጊዜ ወይም በዩኒቨርሲቲው የሥርዓተ-ፆታ ክፍል የቀረቡ አቤቱታዎችን አስቸኳይነት መሠረት በማድረግ በሚያቀርበው ጥያቄ ሊሰበሰብ ይችላል።

11.2. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሣኔ ሃሣብ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ ድምፅ እኩል በኩል የተከፈሉ እንደሆነ የሰብሳቢዋ ወይም ሰብሳቢዋ በማትኖርበት ጊዜ በሰብሳቢዋ የተወከ ሰብሳቢ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

11.3. የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤን 4 አባላቱ ከተገኙ ይሞላል የተወከሉ ሌሎች የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶችን በሚመለከት በልምድ ተቀባይነት ያላቸውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶች ይከተላል።

11.4. የኮሚቴው ሰብሳቢ በማትኖርበት ጊዜ በሰብሳቢዋ በፅሁፍ የተወከለ ሌላ አባል ስብሰባውን ሊመራ ይችላል። ሆኖም ሰብሳቢዋ በጽሁፍ ያልወከለች ከሆነና ከአምስት የስራ ቀናት በላይ የማትገኝ/የማይገኝ ከሆነ ሌላ እስኪመለስ/እስክት መለስ ሰብሳቢ በአባላቱ መመረጥ አለበት። ይህ ሰብሳቢው/ዋ ራሷን በምታነሳበት ጊዜም ይፈፀማል።

11.5. በኮሚቴው የሚጣሩ አቤቱታዎች የመጨረሻ ውሣኔ አግኝተው በማስታወቂያ ስሌዳ እስኪለጠፉ ድረስ በሚስጥር መጠበቅ ይኖርበታል።

### 12. የኮሚቴ አባላት መከተል ስለሚገባቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች፣

12.1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ለኮሚቴ አባልነት ያወቃቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች በሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡

12.2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በውሣኔ የቀረቡ አቤቱታዎች ከራሱ፣ ከቅርብ ጓደኛው ወይም ከዘመዱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ከአባልነት እራሱን ማግለል አለበት፡፡ እራሱን የማያነሳ ከሆነም የኮሚቴው ሰብሳቢ ጉዳዩን ባወቀ ጊዜ ሊያስነሳው ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በኮሚቴ አባላቱ ገለልተኛነት ላይ ቅሬታ ያለው ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ገለልተኛ አይደለም የተባለው ሰው እንደነሳለት ለኮሚቴው ሰብሳቢ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ የኮሚቴው አባላት በሚነሱበት ጊዜ የኮሚቴው አባላት ከምልአተ ጉባኤው በታች የሚሆን ከሆነ በአንቀጽ 7 ከተቀመጡት ጽ/ቤቶች እና ማሕበራት ምክትሎች፣ የሚመረጥ የኮሚቴ አባል ከሆነ ተጠባባቂ ሊተካው ይገባል፡፡

12.3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል አቤቱታዎችን በሚያይበት ወቅት በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ መሠረት ያደረገ አድሎን መፈፀም አይኖርበትም፡፡

12.4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች በኮሚቴው የሚወሰኑ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የጣሰ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚቴውን ሥራ ያደናቀፈ የኮሚቴ አባል ከአባልነቱ መሠረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲስፕሊን ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 13. የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፣

13.1. ማንኛውም የጾታዊ ትንኮሣ እና ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ጉዳዩ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ተቋሙ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አንድ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ ከሆነ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነውን ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

13.3. አቤቱታ አቅራቢው በአካል አቤቱታውን ማቅረብ በማይችልበት ጊዜ በሕጋዊ መንገድ በወከለው ሰው አማካኝነት ማቅረብ ይችላል፡፡

13.4. የአቤቱታ ማመልከቻ መያዝ ስለሚገባቸው ዝርዝሮች፣

ማንኛውም የአቤቱታ ማመልከቻ፣

13.4.1. የከሳሽ ስም

13.4.2. የሚማመርበት የትምህርት ክፍል ወይም የሚሰራበት ክፍል

13.4.3. ድርጊቱ የተፈፀበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት

13.4.4. ተፈፀመ የተባለው የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነት/የድርጊቶ መገለጫዎች

13.4.5. የሚታወቅ ከሆነ የትንኮሳው ፈፃሚ ስምና የትምህርት ክፍል/የሥራ ቦታ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ

13.4.6. የምስክሮች ስም

13.4.7. በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ

13.4.8. የሚጠየቅ ዳኝነት

13.4.9. የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበትን ቀን መያዝ ይኖርበታል፡፡

13.5 የዩኒቨርሲቲው ሥርዓተ ፆታ ጽ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች የያዘ የአቤቱታማመልከቻዎች የሚቀርቡባቸው ቅጾች ማዘጋጀት አለበት፡፡

12.1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ለኮሚቴ አባልነት ያወቃቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች በሚስጥር መጠበቅ አለበት::

12.2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በውሣኔ የቀረቡ አቤቱታዎች ከራሱ፣ ከቅርብ ጓደኛው ወይም ከዘመዱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ከአባልነት እራሱን ማግለል አለበት:: እራሱን የማያገለ ከሆነም የኮሚቴው ሰብሳቢ ጉዳዩን ባወቀ ጊዜ ሊያስነሳው ይገባል:: በዚህ ረገድ በኮሚቴ አባላቱ ገለልተኛነት ላይ ቅሬታ ያለው ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ገለልተኛ አይደለም የተባለው ሰው እንደነሳለት ለኮሚቴው ሰብሳቢ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል:: የኮሚቴው አባላት በሚነሱበት ጊዜ የኮሚቴው አባላት ከምልአተ ጉባኤው በታች የሚሆን ከሆነ በአንቀጽ 7 ከተቀመጡት ጽ/ቤቶች እና ማሕበራት ምክትሎች፣ የሚመረጥ የኮሚቴ አባል ከሆነ ተጠባባቂ ሊተካው ይገባል::

12.3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል አቤቱታዎችን በሚያይበት ወቅት በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ መሠረት ያደረገ አድሎን መፈፀም አይኖርበትም::

12.4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች በኮሚቴው የሚወሰኑ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የጣሰ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚቴውን ሥራ ያደናቀፈ የኮሚቴ አባል ከአባልነቱ መሠረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲስፕሊን ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል::

## 13. የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፣

13.1. ማንኛውም የጾታዊ ትንኮሣ እና ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ጉዳዩ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ተቋሙ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል::

13.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አንድ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ ከሆነ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነውን ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል::

13.3. አቤቱታ አቅራቢው በአካል አቤቱታውን ማቅረብ በማይችልበት ጊዜ በሕጋዊ መንገድ በወከለው ሰው አማካኝነት ማቅረብ ይችላል::

13.4. የአቤቱታ ማመልከቻ መያዝ ስለሚገባቸው ዝርዝሮች፣

ማንኛውም የአቤቱታ ማመልከቻ፣

13.4.1. የከሳሽ ስም

13.4.2. የሚማመርበት የትምህርት ክፍል ወይም የሚሰራበት ክፍል

13.4.3. ድርጊቱ የተፈፀበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት

13.4.4. ተፈፀመ የተባለው የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነት/የድርጊቶ መገለጫዎች

13.4.5. የሚታወቅ ከሆነ የትንኮሳው ፈፃሚ ስምና የትምህርት ክፍል/የሥራ ቦታ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ

13.4.6. የምስክሮች ስም

13.4.7. በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ

13.4.8. የሚጠየቅ ዳኝነት

13.4.9. የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበትን ቀን መያዝ ይኖርበታል::

13.5 የዩኒቨርሲቲው ሥርዓተ ፆታ ጽ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች የያዘ የአቤቱታማመልከቻዎች የሚቀርቡባቸው ቅጾች ማዘጋጀት አለበት::

## 14. ለኮሚቴ አባላት፣ ለከሳሽና ለምስክሮች የሚደረግ ጥበቃ

ማንኛው የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ በዚህ መመሪያ መሰረት ከሳሽ ወይም ምስክር ሆኖ ለቀረበ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት የኮሚቴ አባል ሆኖ ለተመደበ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም ድ ጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኝ ያደርጋል ።

## 15. አቤቱታ ማቅረብ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች

15.1. በአንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሰው የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ፣

15.2. ቀደም ሲል ጉዳዩ በዚሁ አካል የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ፣

## 16. አቤቱታ የቀረበበት ሰው የመደመጥ መብት፣

16.1. ማንኛውም በወሲባዊ ትንኮሣ ተግባር አቤቱታ የቀረበበት ሰው የቀረበበትን አቤቱታ የማወቅ፣ ራሱን የመከላከልና የመደመጥ መብቱ የተጠበቀ ነው::

16.2. ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ከቀጠሮ 10 ቀናት በፊት አቤቱታ ለቀረበበት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት::

## 17. የቅጣት እርምጃ አወሳሰድ፣

17.1. ኮሚቴው አቤቱታ በቀረበለት በ20 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ የውሣኔ ሃሣቡን ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዚዳንት ማቅረብ አለበት::

17.2. የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዚዳንት ኮሚቴው የውሣኔ ሃሣቡን ባቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል።

17.3. የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዚዳንት ከኮሚቴው የቀረበለትን የውሣኔ ሃሣብ ለማጽናት ወይም ለመሻር ወይም ለማሻሻል ወይም ከኮሚቴው የውሣኔ ሃሣብ የተለየ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል::

17.4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በአቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከማቅረቡ በፊት የወሲባዊ ትንኮሳው እንዲቆም የሚያደርጉ ጊዜያዊ ትዛዞች ሊሰጥ ይችላል:: (እዚህ ላይ ማለት የተፈለገው ትንኮሳውን ነው እንጅ ክሱን አይደለም)

## 18. ይግባኝ

18.1. በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 81 ለአስተዳደርና ድ ጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የተቀመጠው የይግባኝ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት የተከሰሰና የተቀጣ ማንኛውም የዩቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል በአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዚዳንት የቅጣት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ማቅረብ ይችላል።

18.2. ሴኔቱ ይግባኙ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን መርምሮ ውሣኔ መስጠት አለበት::

## 19. የቅጣት ሪኮርድ መቆያ ጊዜ

19.1. ቀላል ትንኮሳ የፈፀመና የተቀጣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል የጥፋት ድርጊቱን ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ለሁለት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል።

19.2. ከባድ የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት የፈፀመና የተቀጣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል ለአምስት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል።

## 20. እገዳ

20.1. አቤቱታ የቀረበበት ሰው ፈፀመ የተባለው ድርጊት ከባድ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ከሆነ እና የግለሰቡ መኖር በዩኒቨርሲቲው ሆነ በሌሎች ላይ ከፍተኛ ችግር ያደርሳል ብሎ ካሰበ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ከስራ እና ከደሞወዝ ሊያግደው ይችላል::

20.2. አቤቱታ የቀረበበት ሰው ከስራ ካልተሠናበተ በእግዱ ወቅት ያልተከፈለው ደመወዝ ይከፈለዋል::

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. ስለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች

ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል የሚገቡ የስራ ተቋራጮች ወይም ግለሰቦች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቆዩበት
የተለያዩ ስራዎች ለመስራት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል የሚገቡ የስራ ተቋራጮች ወይም ግለሰቦች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዳይተላለፉ በሚገቡት ግዴታ ላይ እንዲካተት መደረግ አለበት።

#### 21.1. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት መፈፀሙን ባወቀ ጊዜ ሪፖርት የማድረግ፣ለምስክርነት ሲጠራ የመቅረብ፣ በእጅም ሆነ በሥራ ኃላፊነቱ የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት የመተባበር ኃላፊነት አለበት።

### 22. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ የወሲብ ትንኮሳ ክሶች ካሉ ቀደም ሲል በተጀመረበት ሁኔታ ተጣርተው ውሣኔ ያገኛሉ።

### 23. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምዶች ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊነታቸው ይቋረጣል።

### 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት ከፀደቀበት ከ-------------------------------ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።